# የኢትዮጵያ ዘውድ ምክር ቤት

THE CROWN COUNCIL OF ETHIOPIA

## ዶክተር አብይ አህመድ ፤ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ምኒስትር ሆነው በመመረጥዎ፤ እንኳን ደስ አለዎት

ከክቡር ልዑል ኤርሚያስ ሳህለ ሥላሴ ኃይለ ሥላሴ፤
የኢትዮጵያ ዘውድ ምክርቤት ፕሬዘዳንት የተሰጠ መግለጫ
ዋሽንግተን ዲሲ፤ መጋቢት 26 ቀን 2010 ዓ.ም

የኢትዮጵያ ዘውድ ምክርቤት፤ ዶ/ር አብይ አህመድ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ምኒስትር ሆነው በመመረጣቸው የተሰማውን ደስታ፤ ሞቅ ባለ መንፈስ ይገልጻል። የዶ/ር አብይ መመረጥ የሚያበስረው፤ በኢትዮጵያ ውስጥ የመንግሥት ስልጣን ከአንዱ መሪ ወደ ሌላው በሰላም መተላለፍ መቻሉን፤ የሀገራችን የፖለቲካና የማህበራዊ ስርአቶች እንደገና ለህዝብ ብሩህ ተስፋ የሚሰጡ መሆናቸውንና እየጠነከሩና የመቻቻል ችሎታቸውን እያዳበሩ መሄዳቸውን ነው።

የዶ/ር አብይን መመረጥ ወቅታዊ ነው ብለን የምናስብበት ምክንያት፤ በሀገራችን ውስጥ ሰላም፤ መረጋጋትና የአንድነት መንፈስ ያመጣል ብለን ስለምንገምት ነው። እርግጠኛ ነን፤ ዶ/ር አብይ ምንም እንኳ ከፊታቸው የተደቀኑባቸው በርካታ ችግሮች ቢኖሩባቸውም፤ እኚህ ኢትዮጵያዊ፤ አንድነት፤ ስምምነት፤ መረጋጋትና የኢኮኖሚ ብልጽግና በሀገራችን ውስጥ ሊያመጡ ይችላሉ ብለን እናስባለን።

የኢትዮጵያ ፓርላማም፤ ስልጣን ከበፊቱ ጠቅላይ ምኒስትር ወደ ዶ/ር አብይ በሰላም ለማስተላለፍ በመቻሉና እኚህን የኢትዮጵያንና የወጣቱን ትውልድ ገናናዊነት ለማብሰር የሚያስቡ ሰው ለመምረጥ በመቻሉ ሊመሰገን ይገባዋል።

የጠቅላይ ምኒስትሩን የሹመት መክፈቻ ንግግር ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠው፤ የኢትዮጵያን ታሪካዊ ማንነት እንደገና እውን ለማድረግ እንደዚሁም ከተቃዋሚ ድርጅቶችና በውጭ ሀገር ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ጋር ለመወያየትና ህብረት ለመፍጠር የሚጥር ራዕይ በመሆኑ ነው። ዶ/ር አብይ በሚመሩት አስተዳደርና በኢትዮጵያውያን ድጋፍ፤ አስፈላጊ የሆኑ የፓለቲካ ለውጦችን፤ የአንድነት መንፈስንና የአኩሪ ህዝቦቻችንን ተስማምቶ የመኖር ችሎታ፤ በሀገራችን ውስጥ ለማምጣት እንዲችሉ እንጸልይላቸዋለን።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር።